# ራስዎን ለመጠበቅ ማወቅ የሚኖርብዎ ነገር

ኤችአይቪም ሆነ ሌሎች ኢንፌክሽኖች የየትኛውንም አገር ሰው ሊያጠቁ ይችላሉ፡፡ ስለ እነዚህ ኢንፌክሽኖች ይበልጥ ባወቁ መጠን ራስዎንም ሆነ ሌሎች ሰዎችን ይበልጥ ከችግሩ መጠበቅ ይችላሉ፡፡





## ተጨማሪ መረጃ

የመድብለ-ባሕል የጤናና የእገዛ አገልግሎት (Multicultural Health and Support Service - MHSS) አገር ቀይረው ለመጡና ለስደተኞች እገዛ የሚሰጥ ነጻና ምሥጢር የሚጠበቅበት አገልግሎት ነው፡፡

በሚከተሉት መንገዶች ልንረዳዎ እንችላለን፡-

- ማንኛውንም ጥያቄዎን በመመለስ
- የኢንፌክሽን ምርመራ እንዲያደርጉ አብረንዎ በመሄድ
- ከጤና አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመርዳት
- የእርስዎና የቤተሰብዎ ደህንነትና ጤና የተጠበቀ እንዲሆን በማገዝ

የማኅበረሰብ ሠራተኞቻችን በስልክ ወይም በአካል አግኝተው ሊያነጋግሩዎ ይችላሉ፡፡ እንደ ምርጫዎ ከወንድ ወይም ከሴት ሠራተኛ ጋር መወያየት ይችላሉ፡፡

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይደውሉልን ወይም ድረ-ገጻችንን ይመልከቱ፡፡

multicultural health and support service
(03) 9342 9725 | enquiries@ceh.org.au

www.ceh.org.au/mhss.aspx

MHSS የባሕል፣ የዘርና የጤና በተሰኘው ማዕከል የሚካሄድ ፕሮግራም ነው፡፡ ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት የሚያፈልገው የገንዘብ ድጋፍ የተገኘው ከሰብዓዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት ነው፡፡ ስዕላዊ መግለጫዎቹ የቲዳንግ ኮር ናቸው፡

AMHARIC



# ግንዛቤዎን ያስፉ ራስዎን ይጠብቁ ጤናዎን ይጠብቁ

ኤችአይቪ | ሄፓታይተስ | በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች

multicultural health & support service

## ኤችአይቪ/ኤድስ ምንድን ነው ?

ሁሉም ሰው በሰውነቱ ውስጥ ጤነኛ እንዲሆንና ጀርሞችን እንዲከላከል የሚረዳው በሽታን የሚከላከልበት አቅም አለው። ሂውማን ኢሚውኖዴፊሽንሲ ቫይረስ (ኤችአይቪ **Human Immunodeficiency Virus – HIV)** የሚያጠቃው የሰውነትን በሽታን የመከላከል አቅም ነው። አኲየርድ ኢሚውኖዴፊሺየንሲ ሲንድሮም (ኤድስ **Acquired Immunodeficiency Syndrome – AIDS)** ደግሞ የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም በኤችአይቪ

ኤችአይቪ ከአንደኛው ሰው ወደ ሌላው የሚተላለፈው በሰውነት ፈሳሽና በደም አማካኝነት ነው። ሰዎች በኤችአይቪ ከሚያዙባቸው መንገዶች መካከል አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ጥንቃቂ የጎደለው ወሲብ መፈጸም (ያለ ኮንዶም የሚፈጸም ወሲብ)
- አደንዛዥ ዕጽ በደም ሥር ሲወጉ መርፌ በጋራ መጠቀም
- በወሊድና ወቅትና በማጥባት ከእናት ወደልጅ

ኤችአይቪ በመሳሳም፣ በወባ ትንኝ ወይም የመገልገያ ዕቃዎችን በጋራ በመጠቀምና አብሮ በመብላት ዕቃዎችን በጋራ በመጠቀምና አብሮ በመብላት አይተላለፍም።

## ሄፓታይተስ ምንድን ነው?

ሄፓታይተስ በጉበት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ቫይረስ ነው፡ ፡ የተለያዩ የሄፓታይተስ ዓይነቶች ያሉ ቢሆንም ሕክምና ካላገኙ ሁሉም ከባድ ሕመም

**ሊያስከትሉ** ይችላሉ። **ሄፓታይተስ ኤ** የሚተላለፈው በተበከለ ምግብ ወይም ውሃ አማካኝነት ነው።
**ሄፓታይተስ ቢ** የሚተላለፈው በወሲብ፣ በተበከለ ደም ወይም በወሊድ ጊዜ ደግሞ ከእናት ወደ ልጅ ነው።
**ሄፓታይተስ ሲ** የሚተላለፈው በተበከለ ደም ለምሳሌ ያህል የአደንዛዥ ዕጽ መርፌዎችን፣ መላጫዎችን፣ የጥርስ ብሩሾችን ወይም የንቅሳትና የሰውነት መብሻ መሳሪዎችን በጋራ በመጠቀም ነው።

ለሄፓታይተስ ኤ እና ቢ መከላከያ ክትባቶችን መውሰድ የሚቻል ቢሆንም ለሄፓታይተስ ሲ ምንም ዓይነት ክትባት የለውም።

## በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች ምንድን ናቸው ?

በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው የሚተላለፉት በጾታ ግንኙነት፣ በአፍ በሚፈጸም ወሲብ ወይም አንዳንድ ጊዜ በጾታ ብልት ንክኪ ወቅት ነው። ካልታከሟቸው የሰውነት መቆጣትና ሕመም ሊያመጡና ወንዱም ሆነ ሴቷ ልጅ መውለድ እንዳይችሉ ሊያደርጉ ይችላሉ።

በጾታ ግንኙነት በሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች ምክንያት ከሚከሰቱት ምልክቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- ቁስል፣ ውሃ መቋጠር ወይም የጾታ ብልት አካባቢ መለብለብ
- ከወንድም ሆነ ከሴት ብልት የሚወጣ ያልተለመደ ፈሳሽ
- በታችናው የሆድ ክፍል ወይም በቆለጥ አካባቢ (ለወንዶች) የሚሰማ ሕመም
- ከወሲብ በኋላ ያልተለመደ ሕመም ወይም መድማት (ለሴቶች)

አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች ኖረውበትም ምንም ምልክት ላይታይበት ይችላል።



## ራሴን መጠበቅ ይኖርብኛል ?

ራስዎንም ሆነ ሌሎችን በኢንፌክሽን ከመያዝ መጠበቅ የሚችሉባቸው ቀላል መንገዶች አሉ።

- ራስዎን ከኤችአይቪና በጾታ ግንኙነት ከሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች መጠበቅ የሚችሉበት በጣም ውጤታማ የሆነው መንገድ ወሲብ አለመፈጸም (መታቀብ) ነው።
- ወሲብ የሚፈጽሙ ከሆነ ሁልጊዜ ኮንዶም ይጠቀሙ። ኮንዶም የወንዱን ብልት የሚሸፍን ከፕላስቲክ የተሠራ መከላከያ ሲሆን የሰውነት ፈሳሽ ከአንደኛው ግለሰብ ወደ ሌላኛው እንዳይተላለፍ ይከላከላል። ኮንዶሞች ከኤችአይቪ፣ ከሄፓታይተስ ቢ እና ከአብዛኛዎቹ በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች ሊከላከሉልዎ ይችላሉ።
- መርፌ፣ የንቅሳት ወይም የሰውነት መብሻ ቁሳቁሶችን፣ መላጫ፣ የጥርሽ ብሩሶችን ወይም ሌሎች የግል መገልገያዎችን ከሌላ ሰው ጋር በጋራ አይጠቀሙ። ይህም ሄፓታይተስ ቢ እና ሲን እንዲሁም ኤችአይቪን ለመከላከል ይረዳዎታል።

## መመርመር ይኖርብኛል ?

አንድ ዓይነት ኢንፌክሽን ይኖርብኝ ይሆናል ብለው የሚያስቡ ከሆነ መመርመር የሚችሉባቸው ብዙ ቦታዎች አሉ። የኤችአይቪ፣ የሄፓታይተስ እና በጾታ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች ምርመራ ቀላል፣ የማያምም እና ከክፍያ ነጻ ነው። ኢንፌክሽን ካለብዎት በሚመረመሩበት ጊዜ ሕክምና ማግኘት የሚችሉ ከመሆኑም ሌላ ሌሎችንም ከመበከል ይቆጠባሉ።